Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

# በኢንተግሬሽን ትምህርት ኮርስ ለሚሳተፉ ግለሰቦች የተዘጋጀ፣ በአንቀጽ 13፣ 14 የዳታ ጥበቃ መሰረታዊ ደንብ (DSGVO) መሰረት የዳታ ሂደትን የሚገልጽ የመረጃ ጽሑፍ

የኢንተግሬሽን ኮርስ በኢሚግሬሽንና ስደተኞች ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ተቀናጅቶ የሚከናወን ሲሆን፣ ለዚህ የግልና የመንግስት ትምህርት ሰጪ ድርጅቶችን ይጠቀማል፣ § 43 እዝባር 3 ዓረፍተ ነገር 2 የመኖሪያ ሕግ።

ይሄንን ሓላፊነት ለማሟላት ተብሎ የርስዎ የግል ዳታዎች በሚቀጥሉት ጽሕፈት ቤቶች ይመዘገባሉ እንደዚሁም በሂደት ውስጥ ይገባሉ:

- ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለሚቀጥሉት ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑትን የርስዎን የግል ዳታዎች መዝግቦ ያስቀምጣል:
    - በአንድ የኢንተኢግሬሽን ትምህርት እንዲሳተፉ ለመፍቀድ (§ 5 እዝባር 1 የኢንተግሬሽን መምርያ) እንደዚሁም ቢበዛ እስከ 300 የትምህርት ሰዓታት የቋንቋ ትምህርት መድገምን ለመፍቀድ (§ 5 እዝባር 5 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ከኢንተግሬሽን ትምህርት ክፍያ ነጻ ለማድረግ (§ 9 እዝባር 2 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ለመጓጓዣ ክፍያ ድጎማ ለመፍቀድ (§ 4a እዝባር 1 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ለኢንተግሬሽን ትምህርት ከሚከፈለው ክፍያ 50% ለማስመለስ (§ 9 እዝባር 6 የኢንተግሬሽን መምርያ)
- የውጭ አገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት፣ ለስራ ፈላጊዎች መተዳደሪያ የሚከፍሉ፣ በስደተኞች የክፍያ ሕግ መሰረት የሚከፍሉ ወይ ደግሞ የፌደራላዊ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ለርስዎ በትምህርት እንዲሳተፉ ፈቃድ ሲሰጡ ወይ ደግሞ እርስዎን ሲያስገድዱ፣ እነዚህ ጽሕፈት ቤቶች ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የርስዎን የግል ዳታዎች ይልካሉ፣ በተለይም የመሳተፍ ፈቃድ ማረጋገጫ ዳታዎችና ለፈተናና መመዝገቢያ የሚተላለፉ ዳታዎችን ይልካሉ። እነዚህ ዳታዎች ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የሚተላለፉት በተለይም ለኢንተግሬሽን ትምህርት ክፍያና ክንውን አስፈላጊ ሲሆኑ ነው (§ 88a እዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 1 የመኖሪያ ሕግ)።
- ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት እርስዎን በ § 7 እዝባር 3 ወይም 5 የኢንተግሬሽን መምርያ መሰረት በአጭር ጊዜ ውስጥ በትምህርት እንዲሳተፉ በአንድ የትምህርት ሰጪ ድርጅት ከመደበዎት ወይም ወደ አንድ የትምህርት ሰጪ ድርጅት ከላከዎት፣ ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለትምህርት ሰጪ ድርጅቱ መረጃ ይሰጣል እንደዚሁም (እርስዎን የሚመለከት ከሆነ) እርስዎን በትምህርት እንዲሳተፉ ላስገደደ አካል መረጃ ይሰጣል።
- ስርዓቱን ጠብቀው ትምህርቱን እንደሚከታተሉ ለማረጋገጥ፣ ትምህርቱን ስኬታማ እንደሆነ ወይም ስኬታማ እንዳልሆነ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ለማተም ሲያስፈልግ ወይም ክፍያንና ክንውንን በሚመለከት አስፈላጊ ከሆነ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት፣ ለኢንቴግሬሽን ትምህርት እንደተመዘገቡና በኢንቴግሬሽን ትምህርት እንደሚሳተፉ የሚገልጹ ዳታዎችን ይልካል (§ 88a እዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 1 የመኖሪያ ሕግ)።
- በ § 4 a እዝባር 2 የኢንተግሬሽን መምርያ መሰረት የኢንተግሬሽን ትምህርቱን የሚያጅብ የልጆች እንክብካቤ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ የሚንከባከባቸውን ልጆች ስም፣

KNr. 630.154a Amharisch BAMF 01/2020

መጠሪያ ስምና የልደት ዕለትን ይመዘግባል፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ ይሄንን መረጃ የሚሰበስበው በኢሚግሬሽንና ስደተኞች ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለማስፈቀድና ለዚሁም ደረሰኝ ለመጻፍ እንዲጠቀመው ተብሎ ነው።

- በኢንተግሬሽኑ ትምህርት እንዲሳተፉ የተገደዱ ከሆኑና ስርዓቱን ጠብቀው ትምህርቱን የማይከታተሉ ከሆኑ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ፣ እርስዎን በዚህ ትምህርት እንዲሳተፉ ላስገደደ/ዱ ኣካል/ት መረጃ ይሰጣል (§ 88a እዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 2 የመኖሪያ ሕግ)።
- የሚመለከተው የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት፣ ለስራ ፈላጊዎች መተዳደሪያ ለመክፈል የሚመለከተው ኣካል፣ በስደተኞች የክፍያ ሕግ መሰረት ክፍያ ለመክፈል የሚመለከተው ኣካል ካመለከቱ፣ በተለይም ማመልከቻው ኣንድ የመግቢያ ፈቃድ ለመስጠት፣ የኢንተግሬሽን ትምህርት ለመፍቀድ ወይ ደግሞ ለማስገደድ፣ የመሳተፍ ግዴታ መሟላቱን ለመቆጣጠር እንደዚሁም የመኖሪያ ፈቃድ ለማራዘም ተብሎ የቀረበ ከሆነ፣ ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የርስዎን የግል ዳታዎችን ለነዚሁ ኣካላት ይልካል (§ 88a እዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 3 የመኖሪያ ሕግ)።

ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤቱ ራሱ የመዘገባቸውና ከሌሎች ኣካሎች የተቀበላቸውን የርስዎን የግል ዳታዎችን ለመጠበቅና ዋስትና የመስጠት ሓላፊነት ኣለበት።

የፌደራሉ ጽሕፈት ቤት ኣድራሻ:

Bundesamt für Migration und Flüchtlinge

Frankenstraße 210

90461 Nürnberg

በፌደራሉ ጽሕፈት ቤት ዳታዎችን ለመጠበቅ ሓላፊነት ያለው ክፍል ኣድራሻ:

Bundesamt für Migration und Flüchtlinge

- Behördlicher Datenschutzbeauftragter -

Frankenstraße 210

90461 Nürnberg

የርስዎ ስም፣ ያባት ስምና የልደት ዕለት ቢዘገይ የኢንተግሬሽኑን ትምህርት ከጨረሱበት ጊዜ ጀምሮ ከኣስር ዓመት በኋላ፣ የተቀሩት የግል ዳታዎች ደግሞ ቢዘገዩ ከኣምስት ዓመት በኋላ ይሰረዛሉ (§ 8 እዝባር 6 የኢንተግሬሽን መምርያ)

በርስዎ የግል ዳታዎች የሚካሄደው ሂደት፣ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የርስዎን ወይ ደግሞ የሌላውን ዋስትና ፍላጎት የሚገድቡ እንደሆኑ ማሳመን ከቻሉ፣ የርስዎ የግል ዳታዎች በተገደበ ሁኔታ ሂደታቸው እንዲካሄድ፣ ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ የማቅረብ መብት ኣለዎት። ከዚህ በኋላ ሂደቱ የሚካሄደው፣ ለሂደቱ የመንግስት ፍላጎት ከዚህ ያመዘነ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በተረፈም የርስዎ የግል ዳታዎችን የሚመለከት መረጃ የመጠየቅና የማረም መብት ኣለዎት እንደዚሁም በርስዎ ዳታዎች ኣለኣግባብ የተካሄደ ሂደት ከኖረ፣ የማሰረዝ መብት ኣለዎት።

ከዚህ በተረፈም ዳታዎች ለመጠበቅ ሓላፊነት ላለው ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት ኣቤቱታ የማቅረብ መብት ኣለዎት:

Bundesbeauftragte für den Datenschutz und die Informationsfreiheit

Husarenstraße 30

53117 Bonn